# International Ethiopian Woman Organization IEWO

# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ)

<u>የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ) አመራር ባደረጋቸው ስብሰባዎች የተደረሰ ውሳኔ</u> ፡-

*እንደሚታወቀው በዓኢሴድ የመወያያ መድረክ ላይ አለመግባባት ከተፈጠረ ቦኋላ በዓኢሴድ ስም ሌላ የመወያያ መድረክ በአንድ የአመራር አባል መከፈቱ ለሁሉም ግልጽ ነው።*
*በድርጅታችን ውስጥ የተከሰተውን ችግር ለመፍታት ይቻል ዘንድ የአመራር አባላት በሞላ ችግሩ በተከሰተበት እለት የተቀዱ መረጃዎችን ለማዳመጥና ውሳኔ ለመስጠት 2 ወር ፈጅቶበታል።*

*ዓኢሴድ በሬድዮም ሆነ በድረ ገፅ የውይይት መድረክ ብዙ ጥሩ ነገሮችን ሰርቷል። ሆኖም ግን ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ተወያይቶ መፍትሄ ከመፈለግ ወደ ሌላ ፅንፍ እርምጃ ድርጅቱን ወደሚያዳክም መሄድ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ሳያጤኑት ቀርተው አይመስለንም።*

*ችግሩ የሚመለከታቸው ሁለተኛ የዓኢሴድ የመወያያ መድረክ የከፈቱት ዶክተር አበባ ፈቃዴ ለመነጋገርና መፍትሄ ለመሻት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የዓኢሴድ ምክርቤት የሚቀጥለውን ውሳኔ አስተላልፏል።*

*ዶክተር አበባ ፍቃዴ የዓኢሴድ የአመራር አባልና እንዲሁም የድርጅቱ ቃል አቀባይ ሆነው ሲሰሩ እንደነበሩ የሚታወስ ነው። ሆኖም ግን በማን አለብኝነት ሌላ የዓኢሴድ መወያያ መድረክ ያለ አመራሩ ፍቃድ መከፈቱን አመራሩ ተወያይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ሀሳቦች ሲያቀርብ የአመራሩን ውሳኔ እንደማይቀበሉ በንቀት መንፈስ አስታውቀው ስብሳእባውን ጥለው ወጥተወል።*

*በተጨማሪም የዓኢሴድን ሬድዮ እንደ ግል ንብረታቸው በመቁጠር አመራሩ ያልተነጋገርባቸውና ያልወሰነባቸው በግላቸው እንደፈለጉት የሚጠቀሙበትና የሚያሰራጩበት ከመሆኑም በላይ ከሌሎች የግል የሬድዮ ጣቢያዎች ጋር ትብብር በሚል መግለጫ በዓኢሴድ ሬድዮ ሲያስነብቡ ተሰምተዋል።*

ስለሆነም የዓኢሴድ አመራር አባላት ዶክተር አበባ ድርጅቱን እንዲሁም አባላቱንና አመራሩን ከምንም ባለመቁጠር እንደፈለጋቸው የሚሰሩ መሆናቸውን አጢኖ

1. ዶክተር አበባ የዓኢሴድ ሬድዮና ሌሎች የድርጅቱ የሆኑ መገልገያዎችና ንብረቶች ለዓኢሴድ እንዲያስረክቡ።
2. በዓኢሴድ ስም የሚያደርጉዋቸውን እንቅስቃሴዎችም በአስቸኳይ እንዲያቆሙ ውሳኔ አስተላልፏል
3. ይህ የዓኢሴድ ምክርቤት ውሳኔዎች ለህዝቡ ይፋ እንዲደረግ በተጨማሪ ወስኗል

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!
ዓኢሴድ ይጠናከራል !!!

የ ዓኢሴድ አመራር
አስቴር ደመቀ
መብራት ሃይለ